# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር **146** የካቲት 24 2003 ገጽ 1


**. . . የህዝባዊው ንቅናቄ ግንባር ቀደም ታጋዮች ወጣቶች መሆናቸው የማይቀር ቢሆንም ንቅናቄዉ የወጣቶች ጉዳይ አድርጎ መፈረጅ የተሳሳተ ይሆናል:: የኑሮ መሻሻል፣ የመብት እና የክብር ጥያቄዎች የመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጥያቄዎች ናቸው:: በመሆኑም በእድሜ፣ በፆታ፣ በሃይማኖት፣ በብሄርም ሆነ በሥራ ዓይነት ሳንለያይ በህዝባዊ ትግሉ መሳተፍ የዜግነት ግዴታችን ሊሆን ይገባል::**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የአድዋ ድል መታሰቢያ ቀን ዘረኛውን የወያኔ አምባገነን አገዛዝ ለማስወገድ ቃል የሚገባበት ነው ተባለ

የግንቦት ሰባት ዘጋቢ በአዲስ አበባ ከተማ ተዘዋውሮ ያነጋገራቸው ወጣቶች የዘንድሮው የአድዋ ድል መታሰቢያ ለነጻነታቸው ቀናይ የሆኑት አያት ቅድሜ አያቶቻችን በጣሊያን ፋሽስት ጦር ላይ የዛሬ 115 አመት ያገኙትን ድል 20 ዓመት ሙሉ በጫንቃችን ላይ ሆኖ የወደፊት ተስፋችንን በማጨለም በባርነት እየገዛን ባለው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ላይ ለመድገም ለራሳችን ቃል የምንገባበት እለት ይሆናል በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል::

ኢትዮጵያዊያን የውጭ ጠላቶቻቸውን አሳፍረውና አዋርደው የሃገራቸውን ታሪክ ካስጠበቁባቸው ጊዚያቶች አንዱ የአድዋ ድል እንደሆነ ያውሱት አስተያየት ሰጪዎች፣ በዘር በሃይማኖት በጎሳና በልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞች ኢትዮጵያዊያንን በመከፋፈልና ርስ በርስ በማጋጨት እድሜውን እስከዛሬ ድረስ አራዝሞ የሚገኘው የዘረኛው አምባገነን አገዛዝም ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከኢትዮጵያዊያን ትከሻ ላይ የሚወርድበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን ተናግረዋል::

ይህ በንዲህ እንዳለ በሰሜን አፍሪቃ ተቀጣጥሎ የአህጉራችንን አምባገነኖች እያስጨነቀ የሚገኘው የአብዮት ማእበል ያስደነገጠው የወያኔው ዘረኛ አምባገነን አገዛዝ አብዮት ለማስነሳት ትሰራላቺሁ በማለት ሰዎችን እያስፈራራና እያሰረ እንደሚገኝ ተያይዞ የደረሰን ዜና ያስረዳል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት የፍሪኩዌንሲ ለውጥ አደረገ:

በቱንዚያ የተቀጣጠለው የህዝብ አብዮት በርካታ ሃገራትን እንደ እሳት እየለበለበ መሆኑ እንቅልፍ የነሳው የወያኔው አምባገነን አገዛዝ ዓለም አቀፉን ታዋቂ የዜና አውታር አልጃዚራን ጨምሮ በርካታ መገናኛ ብዙሃንን ኢትዮጵያዊያን እንዳይከታተሉ እያደረገ እንደሆነ በተደጋጋሚ መገለጹ ይታወሳል:: ከነኝህ የብዙሃን መገናኛ አውታሮች ውስጥ በአጭር ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያዊያን ከፍተኛ አድናቆትና ተቀባይነት እያገኘ የመጣው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ሲሆን የወያኔው አገዛዝ አሁንም ኢሳትን ለማፈን ተደጋጋሚ ጥረት በማድረጉና አልፎ አልፎም በኢሳት ስርጪት ላይ መቁአረጥ በመከሰቱ፣ ለቺግሩ መፍትሄ ይሆን ዘንድ የፍሪኩየንሲ ለውጥ ለማድረግ መገደዱን ኢሳት አስታውቁአል።

አፋኙ አገዛዝ በሃገሪቱ በሚሊየኖች የሚቆጠሩ ዜጎች አሁንም በርሃብ አለንጋ እየተገረፉ ባሉበትና ሃገሪቱም ውስጥ በርካታ የመሰረተ ልማት አውታሮች ወደሁዋላ በቀሩበት ሁኔታ በሚሊየኖች የሚቆጠር ገንዘብ እያፈሰስ እነኝህን የዜና አውታሮች የማፈን ተግባር እየሰራ መሆኑ በተደጋጋሚ መዘገባችን ይታወቃል::

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በመረጃ ምንጮች ላይ የሚወስደውን አፈና አስመልክቶ አስተያየታቸውን በስልክ የገለጹልን አንድ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ እንደገለጹት አምባገነኖች እስከ መጨረሻዋ ደቂቃና ነፍሳቸው እስክትወጣ ድረስ መንፈራገጣቸውን አያቆሙም፣ ለምሳሌ ያክል ሙአመር ጋዳፊ እጂግ በርካታውን ህዝብና የሃገሪቱን ክልል ተነጥቆ በሚገኝበት ሰአትና ሁኔታ ህዝብ ይወደኛል፣ ህዝብ ከኔ ጎን ቆሙአል እያለ እንደሚያወራ አውስተው ወያኔም ቢሆን የልማት መንግስት ነኝ ህዝብ የልማት ስራ እየተሰራለት ነውና ይወደኛል በማለት አሁንም በቁጥጥሩ ስር በሚገኙት መገናኛ ብዙሃን እንደሚለፈልፍ ገልጸዋል። ቀጥለውም ይህ ባዶ ልፍለፋው ከንቱ እንደሆነ የተረዳው የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ሃቀኛና እውነተኛ ዜና የሚያቀርቡ ብዙሃን መገናኛዎችን በንቃት እየተከታተለ መሆኑን፣ የወያኔ የሚዲያ አፈናም መረጃን ከማግኘት እንደማያግደው እምነታቸው መሆኑን ገልጸዋል። በኢሳት መግለጫ መሰረት አዲሱ የስርጭት ፍርኩየንሲ የሚከተለው ነው

**ESAT changes Satellite** Intelsat 10
68.5 East, **C** band
Transponder 14
Frequency: 3805.5 MHz
Polarization: Vertical
Symbol rate: 6670 Msyb
FEC: 3/4

## ግዜ

## የማሌዢያው ፔትሮናስ ኩባንያ የነዳጅ ቁፋሮ ሥራውን ዘግቶ ጓዙን ጠቅልሎ ወጣ

ፔትሮናስ የነዳጅ ቁፋሮ ኩባንያ ኢትዮጵያ ውስጥ በኦጋዴን ክልል አካባቢ ጀምሮት የነበረውን የነዳጅ ቁፋሮ ስራ በማቋዋረጥና ፕሮጀክቶቹንም ለዘረኛው አምባገነን አገዛዝ በማስረከብ ቦታውን ለቆ መውጣቱን ለአገዛዙ ቅርበት ያላቸው ምንጮቻችን ከስፍራው ባስተላለፉልን ሪፖርት ለማወቅ ተችሎአል።

ወያኔ ነዳጅ እያወጣሁ ነው በማለት ህዝቡን በባዶ ተስፋ የሚደልልበት ይህ በ ኦጋዴን ያለው የነዳጅ ቆፋሮ ሥራ በጸጥታ ምክንያት ከተስተጓጎለ የሰነበተ ቢሆንም በአካባቢው ሰላም ያለ ለማስመሰል ዜናው ለህዝብ ይፋ እንዳይሆን ተደብቆ የቆየ መሆኑ ይታወቃል። የማሌዥያው የፔትሮናስ ኩባንያ የተፈጥሮ ጋዝ ክምችት የሚገኙባቸውን የካሉብና የሂላላ መሬቶችና ሌሎች በኦጋዴን ክልል የሚገኙ የነዳጅ ፍለጋ ቦታዎችን ያለምንም ችግር እያከናወነ ነው በማለት ወያኔ በመገናኛ ብዙሃን በርካታ ሰዎችን እያደናገረ በቢዙ ሚልዮን ብር የሚገመት አክስዮን እንደሸጠ ሲታወቅ ሽያጩን የሚቆጣጠሩት የወያኔ የቅርብ ሰዎች እንደሆኑ ለማወቅ ተችሎአል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የፖሊስ ኮሚሽን ህዝብ ግንኙነት ሃላፊ ኮማንዳር ደምሳሽ ሃይሉ በወያኔ ዘረኛነት ተማርረው ከሃገር ኮበለሉ

የዘረኛውና አምባገነኑ ወያኔ አገዛዝ የፌደራል ፓሊስ ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ሐላፊና የአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዝዳንት የነበሩት ኮማንደር ደምሳሽ ሃይሉ በወያኔ ዘረኛነት ተማረው ስራቸውንና አገራቸውን ለቀው በስደት እንግሊስ አገር መግባታቸው ታወቀ::

ኮማንደር ደምሳሽ ሃይሉ በግንቦት ሰባት ስም በመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ከተከሰሱ የአማራ የጦር መኮንኖች ጋር የቀረበ ግንኙነት አላቸው ተብለው በወያኔ የደህንነት ሠራተኞች በአይነ ቁራኛ የሚጠበቁ እንደነበሩ ቢታወቅም ከጥቂት የአማራ መኮንኖች ውጪ ሌሎች የሥርዓቱ ታማኞች ናቸው እንዲባሉ ብቻ የጸረ ሽብርተኝነት ዘመቻ ግብረሃይል ቃል አቀባይ ሆነው ስለግንቦት 7 እስረኞች በሬዲዮና ቴለቪዥን መግለጫ እንዲሰጡ ሲደረግ እንደነበር ይታወሳል።

ኮማንደር ደምሳሽ ሃይሉ የወያኔን አገዛዝ ባገለገሉባቸው በርካታ አመታት የትግራይ ጉጂሌ አባላት የሆኑት የፖሊስ እና የጦር መኮንኖች በሚያሳዩት ዘረኛ አሰራር እጅግ ሲማረሩ እንደቆዩ የሚናገሩ የብ አዴን መረጃ ምንጮቻችን፤ የጸረሽብር ዘመቻ ቃል አቀባይ ሆነው ያገለግሉ በነበረበት ወቅት ሳይቀር በሽብርተኝነት ሥም ስለሚታሠሩም ሆነ ኢላማ ስለሆኑ ሰዎች ከርሳቸው ይልቅ በማዕረግና በደረጃ ከርሳቸው የበታች የሆኑ የትግራይ ተወላጅ የበለጠ መረጃ ያገኙ እንደነበር ይናገራሉ። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የወያኔ የማሟያ ምርጫ ላይ የአዲስ አበባ ህዝብ ድርሽ ሳይል ቀረ። የካድሬዎች ውትወታና ልመና ጆሮ ዳባ ልበስ ተባለ

ከትናንትና በስቲያ ዕሁድ የካቲት 20 ቀን 2003 ዓም እንዲደረግ ታስቦ በነበረው የማሟያ ምርጫ ተቢዬ የወያኔ ድራማ፡ የአዲስ አበባ ነዋሪ በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ድርሽ ሳይል እንደቀረ የግንቦት 7 ዜና ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከው ሪፖርት አስታወቀ።

ወያኔ የሥልጣን ዕድሜውን ለማራዘም እንደ አገራችን ዘመን አቆጣጠር ከ1985 ዓም ጀምሮ በየአምስት አመቱ ሲያደርገው በነበረው ምርጫ በርካታ ዜጎች በአገዛዙ ካድሬዎችና የደህንነት ሠራተኞች ሊደርስባቸው የሚችለውን ወከባና እንግልት በመፍራት በየምርጫ ጣቢያው በመሄድ ድምጻቸውን ወያኔ ለሚያፈራርቃቸው ካድሬዎች ሲሰጡ የነበረ ቢሆንም፤ እየተባባሰ በመጣው የኖሮ ውድነት፤ ሥራ አጥነት እና የግፍ አገዛዝ ተማረው ከዚህ ሊብስ የሚችል ምድራዊ በደል እንደማይኖር በመገንዘብ ሁሉም ሰው ለዚህ ማሟያ ምርጫ ከቤቱ ለመውጣት እንዳልፈለገ ሪፖርተራችን ያነጋገራቸው የተለያዩ ሰዎች ማረጋገጫ ሰጥተዋል።

መለስ ዜናዊ ባለፈው ግንቦት ወር አካሂዶት በነበረው ምርጫ 99.6 ከመቶ የሆነ የመራጭ ድምጽ እንዳገኘ በአፈቀላጠው ምርጫ ቦርድ ይፋ በሆነ ማግሥት፡ በአዲስ አበባ የሚገኙትን የመንግሥት ሠራተኞችና ድህረ ምርጫ 97 በማህበር ያደራጃቸውን ወጣቶች በማስገደድ ለድጋፍ ሰልፍ መስቀል አደባባይ እንዲወጡና የውዳሴ መፈክር እንዲያሰሙት አድርጎ የነበረ ሲሆን ፡ ላለፈው እሁድ ማሟያ ምርጫ ከሰልፈኞቹ ቁጥር ሲሶው የሚሆን እንኳ በተዘጋጀው የምርጫ ጣቢያ ዝር አለማለቱ የምርጫ ቦርድ ካድሬዎችንና በየወረዳው ተኮልኩለው በጉቦና በምዝበራ ህዝቡን የሚመጠምጡትን የየወረዳ የወያኔ ሹመኞችን ሳይቀር ክፉኛ እንዳስደነገጠ ለማወቅ ተችሎአል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ሊያመልጠን የማይገባ መልካም አጋጣሚ

ሁኔታዎችን በአንክሮ የአስተዋለ ሰው ዛሬ አገራችን ኢትዮጵያ በለውጥ ዋዜማ ላይ መሆኗን መረዳት አያቅተውም፡፡ ህዝብ የለውጡን አይቀሬነት ተቀብሎ አሁን እያስጨነቁት ያሉት "ህዝባዊው አመጽ መቸ፤ የትና እንዴት ይነሳል" የሚሉት ጥያቄዎችን መመለስ ሆኗል፡፡

ከሳምንታት በፊት ባህሬን፣ ሊቢያና የመን በተመሳሳይ ሁኔታዎች ውስጥ ነበሩ፡፡

የባህሬን መሳፍንት የህዝብን ተቃውሞ ለማስቀረት ገንዘብ አደሉ፤ የፓለቲካ ሥርዓት ማሻሻያዎችን እንደሚያደርጉ ቃል ገቡ፡፡ ይህ አልሰራ ሲል ወደ ማስፈራራት ሄዱና ታንኮቻቸውን በጎዳናዎች ላይ አሰማሩ፡፡ ሆኖም ግን ማስፈራሪያዎችም እንደቀድሞው ውጤታማ መሆን አልቻሉም፡፡ ባህሬን አሁን በለውጥ ማዕበል ውስጥ ነች፡፡

የየመኑ ዓሊ ዓብደላ ሳልህ የለውጡን አይቀሬነት አስቀድመው ካሸተቱ አምባገነኖች አንዱ ነው፡፡ ስለሆነም "በከፍተኛ የለውጥ ሂደት ውስጥ ነው ያለነው፡፡ ለወጣቶች በርካታ የሥራ እድሎችን ለመፍጠር እየሠራን ነው፡፡ በሚቀጥለው ምርጫ አልወዳደርም" እያለ ህዝቡን ለማታለል ጥሯል፡፡ እነዚህ ከረፈደ በኋላ የመጡ ማባበያዎች ህዝባዊ አመፁን አላስቀሩትም፡፡ በዚህም ምክንያት ወደለመደው ጉልበት መሸጋገር አስፈለገው፡፡ ጥቂት ደጋፊዎቹን ህዝባዊ ሰልፎችን እንዲበጠብጡ በማድረግ ህዝብን ከህዝብ ጋር ለማጣላት ሞከረ፡፡ ይህ መሰሪ ተግባር ያሰበውን ያህል ባይሳካለትም ለበርካታ ዜጎች ህይወት ማለፍ ምክንያት ሆነ፡፡ ዓሊ ዓብደላ ሳልህ ግን ደስተኛ ነው - የጥቂት ሳምንታት ተጨማሪ የሥልጣን ጊዜ ሰጥቶታልና፡፡ ያም ሆኖ የዓሊ ዓብደላ ሳልህ የስልጣን እድሜ አጭር እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡ በጎሳዎች መካከል በቀሰቀሰው ግጭት የራሱ ጎሳ መሪዎች ሳይቀር አዝነውበታል፣ ከድተውታልምም፡፡

የሊቢያው ኮሎኔል ሞዓማር ጋዳሚ ደግሞ "ለፈጣን እድገት እንቅፋት የሆነብኝን ቢሮክራሲን ለመቃውም እኔም ሰልፍ እወጣለሁ" በማለት ዓለምን አስደምሟል፡፡ "የሊቢያ ህዝብ በሙሉ ይወደኛል፤ ለኔ ሲልም ህይወቱን ይሰዋል" እያለ የሚናገረው ጋዳፊ ለስልጣኑ ሲል ህዝብን በአይሮፕላን ከማስደብደብ እንደማይመለስ በተግባር አሳይቶናል፡፡ የሊቢያ አብዮት መሪ ነኝ የሚለው ጋዳፊ "አንድ ሰው እስከሚቀር ድረስ እንደሚዋጋ፤ ማሸነፍ እንኳን ባይችል አገሪቷን ሶማሊያ ማድረግ እንደማያቅተው" በግልጽ የተናገረ ሰው ነው፡፡ ግን የሱም የሥልጣን እድሜ በየእለቱ እያጠረ ነው፡፡

በአገራችንም በመለስ ዜናዊ የሚመራው የትግራይ ነፃ ነጻ ግንባር ጉጅሌ እያስገመገመ ያለውን የለውጥ ማዕበል በሽንገላ ለመደለል ደፋ ቀና እያለ ነው፡፡ "ለወጣቶች ሥራ እንሰጣለን፤ ተመዝገቡ፡፡ ከሥራ የተባረሩ ሠራተኞችን ወደ ሥራ እንመልሳለን፡፡ የዋጋ ግሽበትን በቁጥጥር ሥር እናደርጋለን ...." የማይለው የለም፡፡ በከፍተኛ ድምፅ ተመርጫለሁ እያለ የሚቀባጥረው ይህ ቡድን ማናቸውም ዓይነት የሰዎች መሰባሰብ ህዝባዊ አመጹን የሚጭርበት እየመሰለው መበርገግ ጀምሯል፡፡ ሥርግና ቀብር ቢቀሩ ደስታው ነው፡፡ የትግራይ ነፃ ጉጅሌ ያልተረዳው ነገር ይህ መሯሯጥ አመጹን እንደማያስቀረው ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ አመጽ እንዳይነሳ እንዲከላከሉ የሚያሰማራቸው ሰዎች ራሳቸው የአምጹን መነሳት የሚናፍቁ መሆናቸው መረዳት አልቻለም፡፡

በግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እምነት የትግራዩ ነፃ ጉጅሌ ህዝባዊው አመጽ እንዳይቀሰቀስ የመከላከል አቅም የለውም፡፡ ስለሆነም አመጹ ባይቀሰቀስ ምክንያቱ የራሳችን ድክመት እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ህዝባዊ አመጹ ከተቀሰቀሰ በኋላ በለውጥ ኃይሎች ቅንጅት ጉድለት ለጥቃት እንዳይመች ካሁኑ መዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

ከሁሉ አስቀድሞ የህዝባዊው ንቅናቄ ግንባር ቀደም ታጋዮች ወጣቶች መሆናቸው የማይቀር ቢሆንም ንቅናቄዉ የወጣቶች ጉዳይ አድርጎ መፈረጅ የተሳሳተ ይሆናል፡፡ የኑሮ መሻሻል፣ የመብት እና የክብር ጥያቄዎች የመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም በእድሜ፣ በፆታ፣ በሃይማኖት፣ በብሄርም ሆነ በሥራ ዓይነት ሳንለያይ በህዝባዊ ትግሉ መሳተፍ የዜግነት ግዴታችን ሊሆን ይገባል፡፡

ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በቅርቡ መቅስቅሱ አይቀሬ የሆነው ህዝባዊ አብዮትን በተመለከተ ህዝባችን የሚከተሉትን ነጥቦች በአንክሮ እንዲያጤን ያሳስባል፡፡

1. ወጣቶች ፍትህ የሰፈነባት እና የበለፀገች ኢትዮጵያን የመገንባት ኃላፊነታቸውን የሚወጡበት መልካም ተፈጥሮላቸዋል፤ ሊያመልጣቸው አይገባም፡፡
2. ጎልማሶችና አዛውንትም ለራሳቸውም፣ ለልጆቻቸው የምትሆን የተሻለች ኢትዮጵያን መሠረት የመጣል እድል አግኝተዋል፡፡ ይህ እድል ሳይጠቀሙበት ሊያልፍ አይገባም፡፡
3. የመከላከያ፣ የፓሊስና የደህንነት ተቋማት ባልደረቦች ከህዝብ ጎን በመቆም የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ወገንተኝነታችሁን የምታስመሰክሩበት መልካም አጋጣሚ ተፈጥሮላችኋል፤ ተጠቀሙበት፡፡
4. ተገዳችሁም ሆነ ተደልላችሁ የወያኔ አገልጋዮች የሆናችሁ ራሳችሁን ነፃ በማውጣት ክብራችሁን የምታስመልሱበት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላችኋል፤ እናንተም ይህንን እድል አታስመልጡ፡፡

ማናችንም ይህ እድል ሊያመልጠን አይገባም፤ እንጠቀምበት፡፡

ይህ ህዝባዊ አብዮት ለተሻለ ኑሮ፣ ለዜግነት ክብር፣ ለነፃነትና እኩልነት የሚደረግ ትግል ነዉና ሁላችንም በጋራ እንነሳ፡፡ መፈክራችንም የአማርኛና ኦሮምኛ ጥምር ቃል "በቃ-ጋዬ" ይሁን፡፡

በቃ -ጋዬ!!!!

---

## የአድዋ ድል መታሰቢያ ቀን ዘረኛውን የወያኔ

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት በዘረኛው አምባገነን አገዛዝ ሃገርን የማጥፋት ስራ የተማረረው የኢትዮጵያ ህዝብ በርግጥም በቴኒዚያና በግብጽ የታየውን ህዝባዊ ማእበል ለማነሳሳት በቂአፍ ላይ ነው። ይህን እንደ እሳተ ገሞራ ሊፈነዳ የተቃረበ የህዝብ ብሶት የተረዳው የዘረኛው አምባገነን ቁንጮ መለስ ዜናዊ አገዛዝ አጋዚ የተባለውን ልዩ የሰራዊቱን ጦር እያሰለጠነና በተለያዩ ቦታዎች እየመደበ እንደሆነ ዘጋቢያችን ካስተላለፈልን ሪፖርት ለመረዳት ተችሎአል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከህዝቡ ጎን በመቆም ዘረኛው አገዛዝ የሚያራምደውን የጥፋት ርምጃ ላይቀበሉ ይችላሉ ተብለው የተጠረጠሩና የተለዩት የሰራዊት አባላት ደግሞ በተለያዩ የሃገሪቱ ክልሎች እንዲበታተኑ እየተደረገ እንደሆነ ታውቁአል ።

በሌላ በኩል ደግሞ የሚይዝና የሚጨብጠውን ያጣው ወያኔ በአዲስ አበባ የተጠናከረ ፍተሻ አጠናክሮ መቀጠሉንና ዜጎችን እያንገላታ መሆኑን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘግቡአል፤፤ እንደ ኢሳት ዘገባ መጋቢት 22 ቀን 2003 በርካታ መኮንኖች በሜክስኮ እና በሳር ቤት አካባቢዎች ተደርድረው ይታዩ እንደነበርና ሾፌሮች ከመኪኖቻቸው እየወረዱና እግረኞችም ማለፊያ ተከልክለው ሲፈተሹ መዋላቸው የተገለጸ ሲሆን ኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ሰአት ያለው ውጥረት በአጭር ጊዜ ህዝባዊ ተቃውሞ ሊፈነዳ እንደሚችል አመላካች ነው ተብሉአል።

## የፖሊስ ኮሚሽን ህዝብ ግንኙነት ሃላፊ ኮማንዳር ደምሳሽ ሃይሉ

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የጎጃም ተወላጅ የሆኑት ኮማንደር ደመላሽ ሃይሉ ወያኔን የተቀላቀሉት በጸረ ደርግ ትግል ወቅት እንደሆነ ይታወቃል። በመለስ ዜናዊ የሚመራው ዘረኝ እና ፋሽስት አገዛዝ በተለይም በአማራና የኦሮሞ ተወላጆች ላይ ይህ ቀረሽ የማይባል በደልን ሲፈጽም እንደቆየ መረጃዎችን በማስደገፍ በተከታታይ ስንዘግብ የቆየን መሆናችን አይዘነጋም። በተለይም በቅርቡ ከወያኔው አምባገነን አገዛዝ ቃሊቲ እስር ቤት ሾልኮ በወጣ መረጃ ዘረኛው አገዛዝ የአማራ እና ኦሮሞ ተወላጅ ላይ የሚፈጽመው ሰቆቃ በቃላት መግለጽ የሚያስቸግር እና ለሂሊና የሚሰቀጥጥ እንደሆነ ስታወቅ የግንቦት 7 እስረኞች በተባሉት አማራ ተወላጇ ላይ በጣም ጸያፍ የሆነ ስድብ ከመጠቀም ጀምሮ ብልት ላይ ጠርሙስ ማንጠልጠልና የዘር ፍሬንም መቀጥቀጥ የመሳሰሉ ዘግናኝ ተግባራትን እየፈጸመ መሆኑ መጋለጡ አይዘነጋም።

ኮማንደር ደምሳሽ በወያኔ ዘረኝነት ከሚማረሩት በርካቶች አንዱ ሲሆኑ ለምን እና እንዴት ከአገር እንደወጡ ወደፊት መረጃ አጠናክረን የምናቀርብ መሆናችንን ከወዲሁ እንገልጻለን።

## የማሌዢያው ፔትሮናስ ኩባንያ የነዳጅ ቁፋሮ

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ፔትሮናስ ፕሮጀክቱን ዘግቶ ከመውጣቱ በፊት ወያኔ የፕሮጀክቱን ሃላፊነት ተረክቦ ለማንቀሳቀስ የሞከረ ቢሆንም በነዳጅ ቁፋሮ ልምድ ማጣትና በሰለጠነ ሰው ሃይል እጥረት ሥራውን ሊገፋበት እንዳልቻለ ለፕሮጀክቱ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ይናገራሉ። ቀደም ብሎ በተደጋጋሚ ባቀረብናቸው ዘገባዎች የኦጋዴን ነጻ አውጪ ግምባር በወያኔ ጦር ላይ ተደጋጋሚ ጥቃት ሲያደርስ መቆየቱን፤ በዚህም ምክንያት ፔትሮናስ ኩባንያ ስራውን በተገቢው መንገድ ለማከናወን ሳይችል መቅረቱን መግለጻችን ይታወሳል። ይሁን እንጂ ከዚህ ዘገባ ጋር በተያያዘ ለአገዛዙ ቅርበት እንዳለው የሚታወቀው ሪፖርተር ጋዜጣ ባለፈው ዕሁድ ህትመቱ ፔቶሮናስ ኩባንያ በራሱ የውስጥ ችግር ምክንያት ፕሮጀክቶቹን ለዘረኛው አገዛዝ ሙሉ በሙሉ አስረክቦ ወጥቱአል ብሉአል።

ፔትሮናስ እ.ኤ.አ ከ2004 ዓ.ም. ጀምሮ በጋምቤላ ክልል የነዳጅ ፍለጋ ሥራ ሲያካሂድ መቆየቱ የሚታወስ ሲሆን፣ ከ2005 ዓ.ም. ጀምሮ ደግሞ በኦጋዴን፣ በገናሌ፣ በወልወልና በፌርፌር አካባቢ ተመሳሳይ ሥራ ሲያካሂድ መቆየቱ ይታወሳል፡፡

ወያኔ ነዳጅ አወጣበታለሁ እያለ ህዝቡን በባዶ ተስፋ የሚደልልበት የኦጋዴን ክልል ህዝብ የወያኔን ዘረኛ አገዛዝ በመቃወም የሞት ሽረት ትግል እያካሄደ የሚገኝበት ክልል ሲሆን ህዝባዊ ተቃውሞውን ለመደምሰስ ወያኔ እየወሰደ ባለው የጅምላ ጭፍጨፋ ሂውማን ራይትስዎች የተባለው አለም አቀፍ የሰብ አዊ መብት ተሟጋች ድርጅት ወያኔን በዘር ማጥፋት ወንጅል መክሰሱ ይታወቃል።

## የሰሜን አፍሪቃ ህዝባዊ አመፆችና ያገራችን እጣ ፈንታ

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ እሁድ ፌብሩዋሪ 13፣ 2011 ዓ:ም. በዳላስ ከተማ ግንቦት ሰባት በጠራው ህዝባዊ ስብሰባ ላይ የቀረበ ንግግር: ክፍል 2 - የመጨረሻ ክፍል

### በህዝባዊ አመፁ ዋዜማ አገራቱ የነበሩበት ሁኔታ . . .

3. **ፀረ-ሽብርተኝነት:** እነዚህ አገሮች በፀረ-ሽብር ትግል የአሜሪካና የአውሮፓ መንግሥታት አገሮች አጋሮች የሆኑ በዚህም ምክንያት የአሜሪካና የአውሮፓ መንግሥታት እንክብካቤና ጥበቃ ያልተለያቸው ናቸው። በተለይም ሙባረክ የአሜሪካ ሁነኛ ወዳጅ መሆኑ የአሜሪካ ከፍተኛ ድጋፍ ሲያገኝ የነበረ ከግብጽ ይልቅ ለአሜሪካ ጥቅም የቆመ ሰው ነበር።
4. **የተቃዋሚዎች መዳከም:** በቱኒዚያና በግብጽ ህዝባዊው ተቃውሞው የፈነዳው የተቃዋሚ ኃይሎች በተዳከሙና በተከፋፈሉበት፤ ህዝብም ውስጥ በከፍተኛ የተስፋ መቁረጥ ስሜት ውስጥ በነበረበት ወቅት ነው።
5. **የኑሮ ሁኔታ ማሽቆልቆል:** የእነዚህ አገራት ውስጥ መንግሥታት ስለ ኢኮኖሚ እድገት ሲሰብኩ የቆዩ ቢሆንም የአብዛኛው ህዝቡ የእለት ተእለት ኑሮ በዋጋ ንረትና በሥራ እድሎች እጦት እያሽቆለቆለ ሄዷል።
6. **ከፍተኛ የሃብት መበላለጥ:** የአብዛኛው ህዝብ የእለት ተእለት ኑሮ እያሽቆለቆለ የየአገራቱ ገዢዎችና ተባባሪዎቻቸው የተንደላቀቀ ህይወት፤ ዓይን ያመጣ ዘረፋና ሙስና ሌላው የጋራ ባህሪያቸው ነበር።

ከላይ ከተዘረዘሩት ነጥቦች አንፃር አገራችን ኢትዮጵያ የምትገኝበትን ሁኔታ ስንገመግም በሁሉም ነጥቦች ከሁሉም በባሳ ሁኔታ ላይ ትገኛለች። ስለሆነም የሰሜን አፍሪካን ህዝባዊ አመጽ የቀሰቀሱት ከላይ በተዘረዘሩት ነገሮች ምክንያት ከሆነ ተመሳሳይ ነገር ኢትዮጵያም ውስጥ የመነሳቱ እድል ከፍተኛ ነው።

ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ በጎጂ መልኩ የምትለይባቸውን አራት ነጥቦችን ማንሳት ያስፈልጋል።

1. **በሥልጣን ላይ ያለው ቡድን ባህርይ።** በአገራችን በሥልጣን ላይ ያለው ገዢ ቡድን ራሱን እንደ አገሪቱ ዜጋ የማያይ፤ ዜጎችም "ወገናችን ነው" ብለው ለመቀበል የሚቸገሩበት ሁኔታ መኖሩ በህዝብና መንግሥት መካከል የፊት ለፊት ግጭት ቢነሳ ወደ ጠቅላላ ውድመት ያመራል የሚል ስጋት በአንዳንድ ሰዎች ውስጥ እንዲኖር አድርጓል፤
2. **የጦር ሠራዊት፣ የፓሊስና የስለላ ተቋማት ዘረኛ በሆነ መንገድ የተደራጁ** በመሆናቸው ህዝቡ በአንድነት እንዳይነሳ እንቅፋት ይሆናሉ፤ ቢነሳም የተቃውሞውን ሲቪል ባህርይ በማሳጣት ዘርን መሠረት ወደ አደረገ ግጭት ያመራ ይሆናል የሚል ትንተናም የሚሰጡ ሰዎች አሉ፤
3. በምርጫ 97 ማግሥት በደረሰት አፈናና በተቃዋሚ ፓርቲዎች መከፋፈል ምክንያት የኢትዮጵያ ህዝብ ተስፋ ቆርጧል፤ ህዝቡ ቢነሳሳም ትግሉ በመሪ እጦት መሰናከሉ አይቀርም የሚል ትንተናም ይሰጣል።
4. በኢትዮጵያ ውስጥ የመረጃ ስርፀት በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ እንደ ቱኒዝያና ግብጽ በTweeter እና Facebook ሰልፉን ማስተባበር አይቻልም የሚል ሃሳብ በተደጋጋሚ ይነሳል።

አራቱም ነጥቦች በተወሰነ መጠን እውነት አላቸው። ሆኖም ግን እነዚህ በኢትዮጵያ ውስጥ ህዝባዊ አመጽ እንዳይነሳ ይከላከላሉ ብዬ በበኩሌ አላምንም።

### ከቱኒዚያና ግብጽ ህዝባዊ አመፆች ትምህርት

1. **የወጣቶች ተሳትፎ:** በቱኒዚያና ግብጽ ህዝባዊ ንቅናቄዎች ውስጥ ወጣቶች ግንባር ቀደም ሚና ተጫውተዋል። እንዲያውም ንቅናቄዎቹ ባለቤት ይኑራቸው ቢባል "የወጣቶች ንቅናቄ" ነው መባል የሚችለው። የቱኒዚያና ግብጽ ወጣቶች ወላጆቻቸው ባስቀመጡላቸው ሥርዓት መኖር አልፈለጉም። ወላጆቻቸው ያኖሩላቸው ሥርዓት ባርነት ነበር። እነሱ ሊኖሩበት የሚፈልጉትን ሥርዓት ወላጆቻቸው ሊገነቡላቸው እንዳልቻሉ ተረድተዋል። እናም ለራሳቸው የሚመኙትን ሥርዓት ራሳቸው ለመገንባት ቆርጠው ተነሱ።

   ኢትዮጵያም ውስጥ ለለውጥ ሌላ ጎዳና ያለው አይመስለኝም። ያለፉት ትውልዶች መልካም ተግባራትን አከናውነዋል። ሆኖም ጀምረው ያልጨረሷቸው እና ጭራሹን ያልጀመሯቸው በርካታ ነገሮች ለአሁኑ ወጣት ተላልፈዋል። የዛሬው የኢትዮጵያ ወጣት ብዙ እዳ ከወላጆቹ መረከቡ እጅግ የሚያሳዝን ነው። የሆነ ሆኖ ወጣቶቻችን አንድ ቁም ነገር መረዳት ይገባቸዋል - ወላጆቻቸው ለእነሱ የሚመች ሥርዓት አልገነቡም፤ አይገነቡምም። ለራሳቸው የሚሆን ሥርዓት መገንባት ያለባቸው ራሳቸው ናቸው። የቱኒዚያና የግብጽ ወጣቶች ኃላፊነት መወሰድ ሲጀምሩ ነው ጉርምርምታ ወደ አመጽ የተሸጋገረው። ወጣቶች በዚህ ትግል ውስጥ ካልገቡ የሚኖረው ማጉረምረም ብቻ ይሆናል።

2. **ፈጠራ፤** የራሱን ነፃነት ያወጀ ትውልድ የፈጠራ ችሎታው ምን ያህል እንደሚጎለብት በተደጋጋሚ የታየ ጉዳይ ነው። በቱኒዚያና ግብጽ ወጣቶች ያለ አንባገነኖች ጣልቃገብነት የሚደራጁበት ነፃነት ስላልነበራቸው ህልሞቻቸውን የሚጋሩባቸው መድረኮች አልነበሯቸውም። የነፃነት መንፈስ በውስጣቸው በሰረፀ ጊዜ ግን ይህ ችግር ህልሞቻቸውን አላጨናገፈውም። ለሌላ ተግባር የተዘጋጁትን Facebook እና Twetter ለዓላማቸው ማስፈፀሚያነት ተጠቀሙባቸው። የሚገርመው ነገር እያጣጣረ ያለው የሙባረክ መንግሥት ኤንተርኔትን የዘጋው ወጣቶቹ በአካል ከተገናኙ በኋላ መሆኑ ነው። ታሂር አደባባይ ማራኪ ያደረገው የወጣቹ ፈጠራ ጭምርም ነው።
   ኢትዮጵያ ውስጥ የኢንተርኔት ስርጭት አነስተኛ መሆኑ የሚያሰጋቸው ወገኖች እምነታቸው ማረፍ ያለበት በወጣቶች የፈጠራ ችሎታ ነው። ወጣቶች አምርረውና ቆርጠው ከተነሱ እነዚህ ችግሮች የሚወጡባቸው መንገዶች አያጡም። [በምርጫ 97 ዋዜማ በአንድ የገጠር ከተማ የወያኔ ደጋፊዎች ሰልፍ ይወጣሉ። ብዙ የንብ ምልክት የታተመበት ወረቀት በየቤቱ ተበተነ። በዚህ የተናደደው ወጣት የአባቱን አንድ የንብ ቀፎ ከነንቦቹ ተሸክሞ "አርማችን ነው" እያለ ሰልፍ ወጣ። ግርግሩ ንቦቹን ረበሻቸውና ሰልፈኛው በመንደፍ ሰልፉን በተኑት። ነፃነት የሚሰማቸው ወጣቶች የሚያመጡት መፍትሄ ይገርማል]
3. **በራስ የመተማመን ስሜት:** ቱኒዚያዊያንና ግብፃዊያን ፍርሃትን ማሸነፍ የቻሉ በራስ የመተማመን ስሜት በመፍጠራቸው ነው። ግብጽ መለዮ ለባሽ ከሆነው የጦርና የፓሊስ ሠራዊት ውጭ 350 000 የሚደርስ ሰላይና ነጭ ለባሽ አላት ተብሎ ይገመታል። ይህ ሁሉ ሠራዊት ግን አመጹ እንዳይነሳ ማገድ፤ ከተነሳም በኋላ ማፈን አልቻለም። በራስ የመተመመን ስሜት መተሳሰብን፣ መተጋገዝን፣ የጋራ ጥቅምን ማስቀደምን ይፈጥራል።
4. **የሚዲያ ሚና፤** ለእነዚህ ህዝባዊ መነሳሳቶች በመጀመሪያ Facebook እና Tweeter ቀጥሎ ደግሞ አልጀዚራና CNN የተጫወቱት ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው። ኢትዮጵያዊያን ከዚህ የምንወስደው ትልቅ ትምህርት አለ። ኢትዮጵያ ውስጥ ተመሳሳይ አመጽ ቢነሳ የትኛው ሚዲያ ነው የሚዘግብልን? በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ያሉት ወገኖቻችንን እርስ በርሳቸው በምን መንገድ ይገናኛሉ። የኢሳትን አይነት ነፃ የሚዲያ ተቋም መኖር ለትግላችን የሚኖረው ፋይዳ አሁን ፍንትው ብሎ ሊታየን ይገባል።
5. **ጽናት፤** በተለይ ግብፃውያን ዓለምን ያስደመመ ጽናት አሳይተዋል። ህዝባዊ እምቢተኝነት ውጤታማ እንዲሆን በጽናት መታገልን ይጠይቃል። በነገራችን ላይ የሙባረክ ደጋፊዎች በፈረስና ግመል መምጣታቸው ራሱ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ከአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ጋር የመፋለማቸው ገላጭ ይመስላል።
6. **መቻቻል፤** ሰዎች ለትላልቅ ዓላማዎች ሲሰለፉ መለስተኛ ቅራኔዎች ፋይዳ አይኖራቸውም። የነፃነት ትግል ግብፃዊያንን አፋቅሯል። በክርቲያኖች ጥበቃ ሞስሊሞች ሲሰግዱ፤ ለክርስትያኖች ቅዳሴ ሞስሎሞች ከለላ ሲሰጡ ማየት ችለናል። የሁለቱም ሃይማኖቶች ተከታዮች በጋራ በየእምነቶቻቸው ለነፃነት ፀልየዋል።
7. **የምዕራባዊያን ድጋፍ፤** ምዕራባዊያን የዓለም ህዝቦች ነፃነታቸውን ቢቀዳጁ እና ዲሞክራሲን ቢያሰፍኑ ደስተኞች ይሆናሉ። ሆኖም ግን ከሌሎች አገራት ህዝቦች ነፃነት የራሳቸውን ደህንነት ያስቀድማሉ። ይህ የአገሮች ባህርይ ነው። ለነፃነታችን በምናደርገው ትግል የዲሞክራሲያዊ አገሮች ድጋፍ ለማግኘት መሬት ላይ ያለው ሁኔታ መቀየር እንዳለበት ቱኒዚያም ግብጽም አረጋግጠውልናል። መሬት ላይ ያለው ሁኔታ ሲቀየር ደግሞ ትላንት እሹሹሩ ያሉትን አምባገነን አንስቶ ከማፍረጥ እንደማይመለሱ በመጀመሪያ ከቱኒዚያው ቤን ዓሊ: ከዚያም ከግብጹ ሙባረክ የተማርነው ትልቅ ቁም ነገር ነው። አምባገነኖቹ የዘረፉትን ገንዘብ እንኩዋን እንዳይበሉ ከመቼው በውጭ ያስቀመጡትን ገንዘብ እንዳያወጡ እንደዘጉባቸው አይተናል::
8. **የሲቪክ ድርጅቶች ሚና፤** በጉልህ ባይዘገብም ሲቪክ ማኅበራት ያደረጉት አስተዋጽኦ ፈጽሞ ሊዘነጋ አይገባም። በርካታ የበጎ አድራጎት ማኅበራት እዚያው እሰልፉ ሜዳ ውስጥ ተፈጥረው ፋፍተዋል። የጤና ባለሙያዎች፣ ጋዜጠኞች፣ የኢፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያዎች በተደራጀ መንገድ አገልግሎት ሲሰጡ ቆይተዋል። የእነዚህ መጠናከር ማኅበራዊ ትስስርን አጠናክራል። በተጨማሪም ዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብት ተማጋቾች በስፋት እንዲቀሳቀሱ የመብትጥሰቶች እንዲመዘገቡ ረድቷል።

### ከካይሮ ወደ አዲስ አበባ

የመብት ረገጣ፣ አፈናና ችጋር ኢትዮጵያ ውስጥ በከፋ ሁኔታ መኖሩ የካይሮው ህዝባዊ አመጽ ወደ ኢትዮጵያ የመዛመት እድሉን ከፍ ያደርገዋል። ኢትዮጵያዊያን ለሰብዓዊና የዜግነት ክብራቸው፣ ለነፃነታቸው፣ ለፍትህና ለተሻለ ህይወት ሲሉ በጋራ መነሳታቸው የማይቀር ነገር ነው። ነገር ግን የአመፃው አነሳስ፣ ፍጥነቱና ጥልቀቱ ከአገር አገር የተለያየ መሆኑ አይቀርም። ስለሆነም ካይሮ ያየነውን ፎቶ ኮፒ አዲስ አበባ ውስጥ አናይ ይሆናል። በሰሜን አፍሪቃ ውስጥ ያየናቸው ህዝባዊ አመጾች በጥንቃቄ ታቅደው የተሰሩ ነገሮች አይደሉም። ሆኖም በመጀመሪያ ሌሎች አገሮች ሰርተው ያሳዩን ነገሮች መኖራቸው እኛን በእጅጉ ይጠቅመናል ብዬ አምናለሁ። ከእነሱ ተምረን፤ ራሳችንን መርምረን የጎደሉንን ለመሙላት እድል አግኝተናል። ይህንን ታሪክ የፈጠረልንን እድል በሚገባ ለመጠቀም በቶሎ ልንፈጽማቸው ይገባሉ ብዬ የማስባቸውን ነገሮች ላንሳ።

1. ኢትዮጵያ በቁጥር ከብዙ እስላማዊ አገሮች የበለጡ ሙስሊም ዜጎች ያሏት አገር ናት፡፡ በሙስሊም ዜጎች ብዛት ኢትዮጵያ ከሳዉዲ አረቢያ፣ ከሱዳን፣ ከአፍጋኒስታንና ከኢራቅ ትበልጣለች፡፡ በዚህም ምክንያት የሙስሊሙን ማኅበረሰብ በስፋት ያላሳተፈ ንቅናቄ ህዝባዊ ሊባል አይችልም፤ ግቡንም አይመታም። የሰሜን አፍሪቃ ሙስሊሞች ለሲቪክ መብቶች መቆም ኢትዮጵያዊያን ሙስሊም ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ያበረታታል ብዬ አምናለሁ። በግብጽ ሞስሊሞችና ክርስቲያኖች በአንድ ላይ መቆማቸው ለኢትዮጵያም ሞስሊሞችና ክርስቲያኖች ትልቅ ትምህርት ነው።

   ወያኔ የኦርቶዶክስና የእስላም፤ የእስላምና የፕሮቴስታንት፤ የኦርቶዶክስና የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮችን እያናከሰ እስካሁን እድሜው አራዝሟል። አሁንም መሠሪ በሆኑ መንገዶች በሃይማኖቶች መካከል ያሉት ግኑኝነቶች እንዲሻከሩ እየተደረገ ነው። በግብጽ እንዳየነው ለሰብዓዊ ክብር፣ ለነፃነትና ለእኩልነት የሚደረግ ትግል የሁሉም ሃይማኖቶች አማኞች የጋራ ትግል ነው። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የሰሜን አፍሪቃ ህዝባዊ አመፆችና ያገራችን እጣ ፈንታ

. . . (ከገጽ 3 የዞረ)

ስለዚህም በተለያዩ ሃይማኖቶች ተከታዮች መካከል ያለው አላስፈላጊ ንትርክ በአስቸኳይ በማቆም ትኩረታችንን በነፃነት ትግሉ ላይ ማድረግ ይኖርብናል። የተፈጠረው ሁኔታ ሙስሊም ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን የነፃነት ትግልን በስፋት እንዲቀላቀሉ ያደርጋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ይህ ሊያመልጠን የማይገባ ትልቅ እድል ነው።

2. ዘረኝነት ለሃያ ዓመታት የወያኔ መንግሥት የፓሊሲ ምሰሶ ሆኗል። የወያኔ ዘረኝነትና ኢፍትሃዊነት ፍጹም ዓይን ያወጣ በመሆኑ ህዝባዊ አመጽ ቢነሳ በፍጥነት ወደ ዘር ግጭቶች ሊያመሩ ይችላሉ የሚለው ስጋት ምንም መሠረት የሌለው አይደለም። በዚህም በተጨማሪ ለነፃነት የምንሰጠው ትርጉምም የተለያየ መሆኑ አንዱ ትልቁ ችግራችን ሆኖ ቆይቷል። በግለሰብ ነፃነት እና በቡድን ነፃነት መነሻነት የተደራጁ ድርጅቶች ተቀራርበው ለመሥራት በመቸገራቸው ሁሉም በወያኔ ለመረገጥ የተመቹ ሆነዋል። በቱኒዝያና በግብጽ የታየው ህዝባዊ አመጽ አገራችን እንዲደርስ ይህ ሲለያየን የቆየው አጥር ፈርሶ በአንድነት መቆም መቻል አለብን። በብሄርም ይሁን በአገር መደራጀታችን ሳይለያየን ለክብራችን፣ ለነፃነታችንና ለተሻለ ኑሮ በጋራ መቆም አለብን።

ወያኔ ሲወድቅ አገር እንደማይፈርስ ብቻ ሳይሆን የተሻለች አገር እንደምትኖረን ለህዝባችን ማረጋገጫ የምንሰጠው ዛሬ በምናሳየው መግባባት፣ መተጋገዝና መተባበር ጥልቀት ነው።

3. የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት የኢትዮጵያ እንጂ የወያኔ ሠራዊት አለመሆኑ እንዲገነዘብ ማድረግ አጣዳፊ ተግባር መሆን ይኖርበታል። ሠራዊቱ ከፓለቲካ ገለልተኛ መሆን ይኖርበታል። ይህንን እውን የማድረግ ሥራ

አሁን ካሉት የወያኔ አዛዦች ትዕዛዝ አለመቀበልንም ሊያጠቃልል ይችላል። የፖሊስና የደህነቱም ክፍል አባላትም አገራዊ ስሜት እንዲኖራቸው፤ እነሱም የነፃነትን ጣዕም እንዲረዱ የመቀስቀሱ ሥራ ተጠናክሮ ሊሰራ ይገባዋል።

4. የፓለቲካ ፓርቲዎችና ሲቪክ ማኅበራት ወያኔን ለመጣል ብቻ ሳይሆን ከዚያ በኋላ የምትኖረዋንም ኢትዮጵያ በጋራ ለመምራት የሚተባበሩ መሆኑን ዛሬውኑ ማሳየት ይኖርባቸዋል። የመንግሥትን ሥልጣን ለመረከብ ብቃት ያላቸው መሆኑን የገዛ ራሳቸውን፣ ሌሎች ድርጅቶችን፡ ህዝብን እና ሌሎች አገራትን ማሳመን ይጠበቅባቸል።

5. የፓለቲካ ፓርቲ መሪዎች ከዘመናዊ የመገናኛ ዘዴዎች ጋር ያላቸውን ቅርበት ማሻሻል ይኖርባቸዋል። የኤለክትሮኒክስ ፖስታዎች (email)፣ Facebook, Tweeter እና ሌሎችንም የኔትዎርክ ዘዴዎችን መፈተሽ ይኖርብናል።

6. አስተማማኝ የሚዲያ ተቋማት መኖር እጅግ አስፈላጊ ነገር በመሆኑ ኢሳትን የማጠናከር ተግባር እንደ አገራዊ ሥራ መወሰድ ይኖርበታል። ከዚህም ሌላ በግልም ሆነ በቡድን የተጀመሩ የሬድዮ ስርጭት አገልግሎቶች የሚቀናጁበት መንገድ ሊፈለግ ይገባዋል።

7. የወያኔን አፋኝ ሥርዓት በትጥቅ ትግል ለመፋለም የተሰለፉ ኃይሎች ብርታት የካይሮዉን ችቦ አዲስ አበባ ለማድረስ ትልቅ ጉልበት ይሰጣል ብዬ አምናለሁ። ስለዚህ በስትራቴጂ ምርጫ ልዩነት ምክንያት የሚነሱ ክርክሮች ቆመው ሁሉም አንድ የጋራ ግብን አስበው ሊንቀሳቀሱ ይገባል እላለሁ።

8. በመጨረሻም ይህ አብዮት ዓለም ዓቀፍ ይዘት ያለው በመሆኑ በትግል ላይ ላሉ በየትም አገር ላሉ ህዝቦች ወገናዊ ድጋፍ መስጠት አስፈላጊ ነው። በተለይ የግብጽ አብዮት ውጤታማ መሆን ወደፊት ለሚመጡት ወሳኝ በመሆኑ ኢትዮጵያዊያን ለግብጽ ህዝብ ያለውን ድጋፍ ማሳየት ይኖርብናል እላለሁ። የአካባቢውና የአለም አምባገነኖች ሙባረክን አይዞህ እንደሚሉት ሁሉ እኛም ታጋዮችን አይዞአችሁ ማለት ይጠበቅብናል።

**ማጠቃለያ**

በሰሜን አፍሪካ ተነስቶ ወደ መላው ዓለም እየተዳረሰ ያለው አብዮት በአይነቱ አዲስ የሆነና ጥልቅ የሆነ እንድምታ ያለው ክስተት ነው። የነፃነት ፍላጎትና ዲሞክራሲ የምዕራቡ ባህል አካል አድርጎ በመውሰድ እኛ ለዲሞክራሱ ያልበቃን አድርጎ ሲመለከት የነበረው አስተሳሰብን ያሳፈረ ክስተት ነው።

ይህ ክስተት ወደ ኢትዮጵያ ሊደርስ ይችላል፤ ስለሆነም መዘጋጀት ይኖርብናል። ዝግጅቶቻችንን በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች መመደብ ይቻላል።

- አንደኛ በውስጣችን ያለውን ልዩነት መቀነስ ይገባናል፤ ቢያንስ የልዩነቶችን ደረጃ መመዘንና ቅደም ተከተል ማውጣት፡ አውጥተንም በዚያ ቅደም ተከተል መሰረት መንቀሳቀስ ይጠበቅብናል።
- ሁለተኛ የሚዲያ አጠቃቀማችን ማሳደግ፡ ማዘመንና በወሳኝ ቁምነገሮች ላይ ማነጣጠር ይኖርብናል፤
- ሶስተኛ የተለያዩ የትግል ስልቶች በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በተግባር ተደጋጋፊ እንዲሆኑ ማድረግ ይጠበቅብናል።

እነዚህን በጊዜ ከከወንን ይህን እጹብ ድንቅ የሆነ አጋጣሚ ተጠቅመን ስብዕናችንን አስከብረን፣ በሰላምና በፍቅር የምንኖርባት አገር እንድትኖረን ማድረግ እንችላለን። አለበለዚያ ግን ሳንጠቀምበት አለፈ ብለን ከምንቆጭባቸው መልካም አጋጣሚዎች አንዱ ይሆናል። ምርጫው በእጃችን ነው።

መፈክራችን **በቃጋዬ** ነው።

ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ።

## ወያኔ ከውጪ ወደ አገር ቤት የሚተላለፉትን መገናኛ ብዙሃንን የማፈን ተግባሩን አጠናክሮ ቀጥሎአል

ሥልጣንን በጠመንጃ ሃይል በመቆጣጠር በህዝባችንና በአገራችን ላይ ይህ ነው ተብሎ ሊዘረዘር ከሚችለው በላይ ወንጀል ላለፉት 20 አመታት ሲፈጽም የኖረው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ከ ዕለት ወደ ዕለት እየደረሰበት ያለውን ህዝባዊ ጥላቻ ለማብረድ ባለመቻሉ ህዝብ ሆ ብሎ እንዳይነሳበት ለመከላከል መገናኛ ብዙሃንን የማፈን ተግባሩን በስፋት እንደቀጠለበት ለማወቅ ተችሎአል።

በሰሜን አፍሪካዊታ አገር ቱኒዚያ የፈነዳውና አምባገነን ሥርዓቶች ያሉበትን አገራት ሁሉ እያዳረሰ ያለው ህዝባዊ አብዮት በአገራችን እንዳይቀጣጠል ለመከላከል በቅርቡ አገልግሎቱን የጀመረውን ኢሳት ለማፈን ወያኔ እየወሰደ ካለው ያልተቋረጠ እርምጃ በተጨማሪ በተለይ ከግብጹ ህዝባዊ አብዮት ወዲህ እያንዳንዱን የመንገድ ላይ አመጽ እየተከታተለ በአረቢኛና እንግሊዜኛ ቋንቋ የሚዘግበውን አልጀዚራ ጭምር በአገራችን ውስጥ እንዳይታይ ለመከላከል ከፍተኛ የሆነ ጥረት እየተደረገ መሆኑ ታውቆአል።

ወያኔ እራሱ ከሳምንታት በፊት ይፋ ባደረገው ስሌት እንኳ ከሁለት ሚሊዮን በላይ የሆነ ወገናችን ለከፍተኛ ረሃብ ተጋልጠ በሞት አፋፍ ላይ ባለበት በዚህ ሰዓት ከ10 እና 20 ሚሊዮን በላይ ዜጎችን ሊመግብ የሚችል ገንዘብ ከመንግሥት ካዝና ወጪ ተደርጎ ነጻ ሚዲያን የሚያፍን ዜመናዊ መሳሪያ ከቻይና በውድ ዋጋ ተገዝቶ አገልግሎት ላይ እንዲውል መደረጉ ወያኔ በህዝባችን ላይ እስካሁን እየፈጸመ ካለው የጭካኔ እርምጃ ትንሹ ነው ተብሎአል። ህዝብ በረሃብ አለንጋ እንደቀጠል ይረግፍ በነበረበት 1977 የድርቅ ወቅት ከአለም አቀፍ ለጋሾች ለትግራይ ተጎጂዎች የተላከውን የዕርዳታ እህል ከፍሉን ለመሣሪያ ግዥ የተቀረውን ደግሞ ተዋጊዎችን ለመመልመል የተጠቀመበት ወያኔ ፡ መረጃን በማፈን የሥልጣን ዕድሜውን ለማራዘም መሞከር የማይጠበቅ እንዳልሆነ ለወያኔ ቅርበት ያላቸው ሁሉ ይስማማሉ።

የሰሜን አፍርካው ህዝባዊ አብዮት ከፈነዳ ወዲህ በወያኔ የአየር ሞገድ ጠለፋ ተጠቂ ከሆኑት መገናኛ ብዙሃን አንዱ ስርጭቱን በ8 መካከለኛና አጭር ሞገዶች ወደ ኢትዮጵያ የሚያስተላልፈው የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ እንደሆነ ለማወቅ ተችሎአል።

## የወያኔ የማሟያ ምርጫ ላይ የአዲስ አበባ ህዝብ ድርሻ

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የሰዎች በማሟያ ምርጫ ጣቢያ ድርሽ አለማለት የረበሻቸው አስመራጮች በአንዳንድ ቦታዎች ከጠዋቱ 5 ሰዓት ጀምሮ ወደየ ነዋሪው ቤት በመሄድ ለምርጫ እንዲወጣ ስወተውቱ እና አላፊ አግዳሚውን ጎራ ብሎ እዲመርጥ ሲለማመጡ መታየታቸውን የገለጸው ዜጋቢያችን፡ እራሱ ለዜና ዘገባ ሊዘዋወር ከቤቱ ወጣ እንዳለ ተጋብዞ እንደነበረና ለምርጫ ተመዝግቦ ካርድ እንዳልወሰደ ቢገልጽላቸውም "ግድ የለም ናና ወዲያውኑ መዝግበን ካርድ እንሰጥህና ትመርጣለ" ተብሎ እንደነበረ ገልጾአል። አንዳንድ ወጣቶች ለአስመራጭነት በየጣቢያው ለተላኩት "እናንተ ውጪ ያሉትን ልታስገቡ ትንንዳንዳላችሁ እኛ ደግሞ ቀደም በለው የገቡትን ሳይቀር ቤቴመንግሥቱን በሃይል ወረረው የያዙትን ገቶቻቸውን ጠራርገን ለማባረር ቀናችንን እየጠበቅን ነው " በማለት በድፍረት ሲናገሩ ተስተውለዋል። የወያኔ ካድሬዎች በሃይል የሚናገራቸውን እና የሚዘልፋቸውን ያለወትሮአቸው በከፍተኛ ትዕግሥት ሲያልፏቸው የተመለከተው ዘጋቢያችን በሰሜን አፍሪካ ለተነሳው ህዝባዊ አብዮት ወያኔ ተረኛ ባለሳምንት መሆኑ ስለገባው ከህዝብ ጋር ላለመጋጨት ስጋት ገብቶት ይሆናል ብሎአል።

በተያያዘ ዜና አዲስ አበባ ውስጥ ዜጎች በወያኔ ሥር ዓት ላይ ለማመጽ እንዲነሱ ጥሪ የሚያደርግ የ ኤስ ኤም ኤስ የስልክ መልዕክት በብዛት እየተሰራጨ መሆኑንና በሌሎች ትላልቅ ከተሞችም ተመሳሳይ የሆነ ጥሪ እየተላለፈ መሆኑን ዘጋቢያችን ከላከው ሪፖርት ለማወቅ ተችሎአል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**

**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እስከ 3:30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2:30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org